እነኋት እናትህ... እነሆ ልጅሽ

ዮሐ 19÷26-27

ክብስልዮስ ዘቂሣርያ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ የተናገራቸውን ቃላት የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ሰባቱ አጽርሐ መስቀል በማለት ይጠሩ ዋቸዋል:: እነዚህም

1. *አባት ሆይ የሚያደርጉትን ኢያውቁምና ይቅር በላቸው*
2. *ዛሬ ከኔ ጋር በገነት ትሆናለህ*
3. *እነኋት እናትህ*
4. *አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ*
5. *ተጠማሁ*
6. *አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ*
7. *ተፈጸመ*

በጌታችን እግረ መስቀል ጌታችንን እጅግ የሚወዱ ሁለት ሰዎች ቆመው ነበር:: እምላክን በማኅፀንዋ የተሸከመች፣ከሄሮድስ ፊት ሸሽታ ለልጇ ስትል የተንከራተተች፣ የተሰደደች፣ ዛሬም በልጅዋ መከራ እጅግ አዝና የቆመች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ጌታን እጅግ በመውደዱ ዕድሜውን በዕንባ የፈጸመው ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ፡ ዮሐንስ ቁጽረ ገጽ ብዙዎች ከአይሁድ የሚደርስባቸውን መከራ ፈርተው ሲሸሹ እስከ መጨ ረሻው ጸንቶ መከራውን ታግሶ የተገኘ ብቸኛው ሐዋርያ::

እሳተ መለኮትን በማኅፀንዋ ለተሸከመች እናቱ ነገረ መለኮትን አምልቶ አስፍቶ የጻፈውን ሐዋርያ ልጇ ይሆን ዘንድ ሰጣት:: ነገረ መለኮትን አምልቶ አስፍቶ ለጻፈው ሐዋርያም እሳተ መለኮትን የተሸከመች ድንግል እናቱ ትሆነው ዘንድ ተሰጠችው::

የእግዚአብሔር ጥበቡ ምን ይረቅ፡ ምንስ ይደንቅ:: ነገረ መለኮት የገባቸው ሰዎች ነገረ ማርያም መልቶ ጐልቶ ይረዳቸዋል:: ይገለጥላቸዋል:: ይሰጣቸዋልም:: እነ ዮሐንስ አፈወርቅ ፣እነ ቅዱስ ቄርሎስ፣እነ አባ ኤፍሬም ሶርያዊ፣እነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣እነ ቅዱስ ያሬድ ነገረ መለኮት ተገልጦላቸው አምልተው አስፍተው አጉልተው የጻፉትን ያህል ነገረ ማርያም ተጨምሮላቸው ፈትፍተው ተንትነው አስረድተዋል::

በዚህ ዓለም በሥጋ ሲገለጥ መጀመሪያ ያየው እርሷን ነበር- እናቱን:: ተፈጸመ ብሎ ሥራውን ሲፈጽምም ያየው እርሷን ነው እናቱን:: የእግዚአብሔር ጥበቡ ምን ይደንቅ::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ሳለ ለሁለት ሰዎች ስጦታ ሰጥቷል:: ለፈያታዊ ዘየማን ገነትን /ለሰው ልጆች ምሕረትን/ ለቅዱስ ዮሐንስ እመቤታችንን /ለእመቤታችን ቅዱስ ዮሐንስን/:: ፈያታዊ ዘየማን ገነትን ያገኘው ጠይቆ ነው:: «ጌታ ሆይ በመንግሥትህ አስበኝ» ብሎ:: እመቤታችን ግን አልጠየቀችም፡ነገር ግን ልጅዋ ወዳጅዋ ምን እንደሚያስፈልጋት ዐወቀ:: የቃናው ተአምር የሚያጠራጥራችሁ ወገኖች ሆይ ይህንን ድንቅ ምሥጢር እዩ:: እንኳንስ «የወይን ጠጅ አልቆባቸዋል» ብላ ለምና ቀርቶ ሳትለምን እንዲ ደረግላት ልጇ መስክሯልና:: ደግሞም የእናቱን ልመና በሰሙም በወርቁም ሲመልስላት ተመልከቱ፡ በጊዜው የሚያልቀውን ወይን ሰጥቶላታል:: «ጊዜዬ አልደረ ሰም» ብሎ የተናገረለት ጊዜው ሲደርስ ደግሞ አማናዊውን ወይን በቀራንዮ አደባባይ ሰጥቶላታል:: ኑ ይህንን ድንቅ እዩ፡ስለተገለጠልን ምሥጢርም ምሥጋና አቅርቡ::

«ለምኑ ይሰጣችኋል፡ ፈልጉ ታገኛላችሁ» ማቴ 6÷7 የሚለው ለዓለም ሁሉ የተሰጠ ነው:: እንዴት ይኼ ይደንቀናል? ፈያታዊ ዘየማን 5500 ዓመት የተዘጋች ገነትን ለምኖ ሲያገኝ እመቤታችን ያልሞላውን ወይን ጠጅ ይሞላ ዘንድ ለምና ታጣለች? ፈያታዊ ዘየማን ለራሱ ለምኖ ሲያገኝ እመቤታችን ለተቸገሩ ለተጨነቁ ለምና ታጣለች?

እመቤታችን በእግረ መስቀሉ ነበረች:: አንዳች ግን አልተናገረችም:: ዓለም በመዳኑ ተደስታለች፡በልጅዋ ስቃይ ግን አዝናለች ፡ ልጅዋ ሉቃስ በወንጌሉ «ማርያም ግን ይህንን ሁሉ ነገር በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር» ሉቃ 2÷20-51 በማለት እንደተናገረላት በዝምታ ችላ ቆመች እንጂ የልቅሶ ድምጽ አላሰማችም:: «በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል» እንዳላት ሉቃ 2÷35 አረጋዊው ስምዖን፡ ከማንም በላይ አዝናለች ግን ዝም አለች:: አርምሞ ትዕግሥት ጠባይዋ ነውና::

ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ ጌታችንን እጅግ ይወደው ነበር:: ጌታችንም የዮሐንስን ልብ ተቀብሎ ለእመቤታችን ሰጣት:: ጌታን ብንወደው ኖሮ የእመቤታችን በሆንን ነበር:: እስከመጨረሻው የጸና እርሱ ይድናል:: ማቴ 24÷13:: ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ እስከመጨረሻው ጸና:: የመዳኑ ምልክት የሆነችውን ድንግልንም አገኘ::

ድኅነትን ፈልገው ይቅበዘበዙ ለነበሩት እሥራኤላውያን «ጌታ ራሱ ምልክትን ይሰጣችኋል፡እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች» /ኢሳ 7÷14/ በማለት ትንቢትን የተናገርክ ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ ሆይ በረከትህ ይደርብን:: እስከመጨረሻው ለሚጸኑ የድኅነታቸው ምልክት እመቤታችን መሆንዋን አይተናልና:: የሰው ልጆች እናት አልባ ሆነው ይኖሩ ነበር:: ሔዋንን እናታችን ማለትንም ትተው ነበር:: ሔዋን ማለት የሕያዋን ሁሉ እናት ማለት ነው:: ነገር ግን እንደስሟ አልሆነችልንም፡የሙታን እናት ሆነች:: የሰው ልጅ ሁሉ ሞት ባንቺ መጣ እያለ ይወቅሳትም ነበር:: አሁን ግን የሰው ልጅ እናትን አገኘ፡ የሕያዋን እናት፡ የሕያዋን ነቢያት፣የሕያዋን አበው፣የሕያዋን ሐዋርያት ፣የሕያዋን ሰማዕታት፣የሕያዋን ጻድቃን፣ የሕያዋን ምእመናን እናት- እመቤታች ንን::

እመቤታችን ጸጋችን ናት፡ ካሣ የተሰጠችን:: ለፈያታዊ ዘየማን ገነ ትን ሲሰጥ ለርሱ ብቻ አይደለም በቀኝ ለሚቆሙ ጻድቃን ሁሉ እንጂ:: ለቅዱስ ዮሐንስ እመቤታችንን ሲሰጥ ለርሱ ብቻ አይደለም፡እርሱን ለሚወዱ ክርስ ቲያኖች ሁሉ እንጂ:: ለዮሐንስ የተገ ለጠ ወንጌል ለዓለም ሁሉ እንደሆነ ለዮሐንስ የተሰጠች እመቤታችንም የተሰጠችው ለዓለም ሁሉ ነው:: ደቀመዝሙሩም ወደ ቤቱ ወሰዳት-ሊያስጠጋት ነውን? አይደለም::

ኤልያስ ወደ ሰራፕታዋ መበለት ቤት ገባ:: የተጠቀመ ማነው? «ዱቄቱ ከማድጋው አልተጨረሰም፡ ዘይቱም አላለቀም» 1ነገ 17÷16 ይህ ቃል የሆነለት ለማን ነው? «በማድጋው ካለው ከእፍኝ ዱቄት በማሠሮም ካለው ጥቂት ዘይት በቀር እንጀራ የለኝም፡ እነሆም ገብቼ ለእኔና ለልጄ እጋግረው ዘንድ በልተነውም እንሞት ዘንድ እንጨት እሰበስባለሁ» ላለችው መበለት አይደለምን? የእግዚአብሔር ታቦት ከቤትህ ያደረ አቢዳራ ሆይ እባክህ ተነሥተህ ንገረን፡ታቦተ እግዚአብሔር በቤትህ በማደርዋ ተጠቀመች ወይስ አንተ በማሳደርህ ተጠቀምክ? «እግዚአብሔር የአቢዳራ ቤቱን ሁሉ ባረከ» 2ሳሙ 6÷11 የተባለ ለአንተ አይደለምን?

አማናዊቷ ታቦት እመቤታችን ወደ አቢዳራ ዮሐንስ ቤት ሄደች፡ትባርከው ቤቱንም ትባርክለት ዘንድ:: እስከ ዕለተ እረፍቷ በቤቱ ኖረችለት:: ማቴዎስ ወንጌ ላዊ ቅዱስ ዮሴፍን «እጮኛው ማርያምን ወሰደ» ማቴ 1÷24 ሲል የተናገረውም ለዚህ ነው:: «ወሰደ» ና «ወሰደ» በትርጉም ይስማማሉ::

የታደሉት በቤታቸው እመቤታችንን ያስተናግዳሉ:: ሥዕሏን በክብር ያኖራሉ ያልታደሉት ደግሞ እንደ አካን የሞታቸው መንሥኤ የሚሆን እርም ያስቀምጣሉ እቴቴውን፣ጨሌውን...እናታችን ሆይ እንደ አቢዳራ ቤት ቤታችንን ኑሮአችንን ባርኪ:: አሜን::

♦♦♦

Scanned by DocumentScanner | Lufick